ተስፋ መቁረጥ ምንድን ነው?

ተስፋ መቁረጥ፡ በነፍስም ሆነ በአዕምሮ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ፍርሃት አዘል ጭንቀት ሲሆን፣ በዚህም ምክንያት አንድ ሰው በዙሪያው ያሉትን ሁኔታዎች የመቀየር እድሉ ላይ ተስፋን እንዲያጣ ይዳርገዋል። ሁሉን ቻይ የሆነው አላህ እንዲህ ይላል: "ሰውንም ከእኛ ችሮታን ብናቀምሰው ከዚያም ከርሱ ብንወስዳት፡ እርሱ በእርግጥ ተስፋ ቆራጭ ከህደተ ብርቱ ነው። [ሁድ፡ 9]"

ተስፋ መቁረጥን ከሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን፡

- አንደኛው፡ በአላህ እዝነት ላይ ተስፋ መቁረጥ ሲሆን፡ በእምነታችን መሠረት የተከለከለ እና የተጠላ ነው።
- ሁለተኛው፡ እየኖርንባት ባለችው ዓለም ወይም በዱንያ ጉዳይ ላይ ተስፋ መቁረጥ ነው።

የተስፋ መቁረጥ ሸሪዓዊ ብይን ምንድን ነው?

1. ተስፋ መቁረጥ በእስልምና የተከለከለ ስለመሆኑ ሁሉን ቻይ የሆነው አላህ እንዲህ ያዘናል "ተስፋ ከሚቆርጡትም መካከል አትሁን። [አል-ሒጅር፡55]"
2. ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ ከእርሱ እና ከእዝነቱ ተስፋ የሚቆርጡትን የጠመሙ እና ከሓዲዎች ብሎ ሲገልጻቸው "እነሆ ከአላህ እዝነት ከሓዲ ሕዝብ እንጂ ተስፋ አይቆርጡም [ዩሱፍ: 87]" ይላል።

በሌላ አንቀጽ ደግሞ፡ "ከጠማማዎች በስተቀር ከጌታው እዝነት ተስፋን የሚቆርጥ ማነው? አለ [አል-ሒጅር፡ 56]"

ዓብደሏህ ኢብን መስዑድ (ረ.ዐ) እንዲህ ብሏል "ሁሉን ቻይ የሆነው አላህ የወሰነልኝን ጉዳይ፡ ምነው እንዲህ ባልሆነ ኖሮ ብዬ ከምናገር ይልቅ፡ ፍም ከሰል እስኪጠፋ ድረስ በአፌ ውስጥ ቢቀመጥ ለእኔ በጣም የተወደደ ነው።

ምክንያቱም ይህንን የሚያደርግ ሁሉን ቻይ በሆነው አላህ ላይ ያለውን አለማወቅ የሚያሳይ ነው። ይህንኑ ሃሳብ ቁርዓን "አዋጅ፡ መፍጠርና ማዘዝ የእርሱ [የአላህ] ብቻ ነው፡ የዓለማቱ ጌታ አላህ በከብሩ ላቀ። [አል-አዕራፍ:54]" በማለት ይገልጸዋል። ይህ ማለት ታዲያ አንድን ነገር የማድረግ ኃይል ያለው በአላህ እጅ ብቻ ነው እንጂ በሰው ልጆች አይደለም ማለት ነው።

ኢብን ሒባን ሀዲስ አል-ቁድሲ ላይ እንደዘገቡት አላህ "እኔ ባርያዬ እንዳሰበኝ ሆኜ አገኝለታለሁ፡ ከልቡ ባሰበኝ እና ባወሳኝ ጊዜም ከጎኑ ነኝ።"

እንዲሁም አሽ-ሸውካኒ እንዲህ ይላሉ "ስለ ጌታው መልካም የሚያስብን ሁሉ፡ አላህ እንዳሰበው ያከናውንለታል፡ ስለ ጌታው መጥፎ የሚያስብን ደግሞ ባሰበው መልኩ ያከናውንለታል።"

የተስፋ መቁረጥ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

1. በነገሮች ላይ መቻኮል። በሕይወት ውስጥ ካሉ ሰዎች እጅግ በጣም አጭር ጊዜን የሚኖሩት፡ ያለቅጥ የሚቸኩሉት መሆናቸውን፡ የተከበረው ቁርዓን ሲነግረን እንዲህ ይላል: "እናም ሰው እኮ ቸኳላ ነበር። [አል-ኢስራእ:11]" እኚህ ሰዎች በቶሎ ተስፋ የሚቆርጡ ዓይነት ሰዎችም ናቸው። ይህ የሚሆነው ደግሞ ነገሮች ባሰቡት እና በተመኙት ልክ እና ፍጥነት ሳይሄድላቸው ሲቀር ነው።
2. ነገሮችን በሰማይ ሚዛን ሳይሆን በምድር ሚዛን መመዘን። አንድ ሰው አንዱን ጥበበኛ እኔ እኮ ጠላቶች አሉኝ በማለት ያናግረዋል፡ ጥበበኛው ያስከትል እና "በአላህም ላይ የሚጠጋ ሰው እርሱው በቂው ነው። [አጥጦላቅ: 3]" ይለዋል፣ ጠያቂው ይቀጥል እና፡ እነሱ እኮ በእኔ ላይ ያሴሩብኛል አለ፡ ጥበበኛው ደግሞ: "ከፉ ተንኮልም በባለቤቱ ላይ እንጂ በሌላ ላይ አይሰፍርም። [አል-ፋጢር: 43]" ብሎ ይመልስለታል፣ ጠያቂው እጅጉን ሥጋት ያደረበት ይመስላል፡ ግን እኮ ብዙ ናቸው ይለዋል፡ ጥበበኛውም እንዲህ አለው "ከጥቂት ጭፍራ

በአላህ ፈቃድ ብዙን ጭፍራ ያሸነፈች ብዙ ናት። [አል-በቀራህ፡ 249]“ ስለዚህ በሕይወታችን የሚያጋጥመንን ማንኛውንም ጉዳይ ሁሉን ቻይ ወደሆነው ወደ አላህ ብቻ ካስጠጋን፡ መቼም ተስፋ አንቆርጥም። ይልቁንስ የቀልባችን ተስፋ ከአላህ ጋር የተቆራኘ ሆኖ ይቀራል። ፈጣሪያችን እኮ በመመለክ ብቸኛ እና አጋር የሌለው እና የነገራቶች ሁሉ አዋቂ ነው! እናም በእርሱ ያመነ ሁሌም በተስፋ የተሞላ ይሆናል።

<u>መልዕክት 2፡</u> ምንም እንኳን በዙሪያው ያሉ ሌሎች ሰዎች እጅግ ተስፋ ቢስ እና በፍርሃት የተዋጡ ሊሆኑ ቢችሉም፣ ይህ በዋነኝነት የእምነት ጉዳይ ነው፤ ስለሆነም እኛ በእስልምና አምነናል የምንል ሰዎች በፍጹም ከተስፋ ቆራጮች ጎራ ራሳችንን ልንመድብ አይገባንም።

እርዳታን ከአላህ ብቻ ፈልግ

ከቁረይሽ ጎሣዎች መካከል ከፊሎቹ የአላህ መልዕክተኛ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ክፉኛ ያስቸግሩ ነበር። ከነሱም መካከል አቡ ላሃብ፣ አል-ሐከም ቢን አቢል-ዓስ ቢን ኡመያ፣ ዑቅባ ቢን አቢ ሙዓይጥ፣ ዑቂይ ቢን ሐምራእ አሰቀፊዩ፣ እና ኢብኑ አል-አስዲእ አል-ሁዘሊይ ቀንዲዎቹ ነበሩ። እነኚህ ሰዎች የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ጎረቤቶች የነበሩ ሲሆን፣ ከነዚህም መካከል ከአል-ሐከም ቢን አቢል-ዓስ በስተቀር እስልምናን ሳይቀበሉ ነበር ያለፉት። ከመካከላቸው አንዱ ነብዩ ሰላት በሚሰግዱበት ወቅት እላያቸው ላይ የበጎችን ጭንቅላት እየወረወረ ያስቸግራቸው ነበር። ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ድንጋይ ስር እስኪደበቁ ድረስ ነበር ዑቅባ ቢን አቢ ሙዓይጥ መከራውን እና ማስቸገሩን የቀጠለው።

ዓብደላህ ቢን መስዑድ (ረ.ዐ) እንደሚናገሩት “ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰላት በካዕባ ዙሪያ ይሰግዱ በነበረበት ጊዜ አቡ ጀህል እና ባልደረቦቹ ደግሞ ተቀምጠው

ይመለከቷቸው ነበር። እርስ በእርስ እየተነጋገሩ እስኪ ከእናንተ መካከል ማነው የግመል ጭንቅላት እምጥቶ፡ ሙሐመድ ሊሰግድ በሚጎነበስበት ጊዜ ጀርባው ላይ የሚያደርግ ተባባሉ። ከመካከላቸው በጣም መጥፎው፡ ዑቅባ ቢን አቢ ሙዓይጥ ወጥቶ አመጣውና ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሲሰግዱ በትከሻዎቻቸው መካከል ጀርባቸው ላይ እስኪያደርግ ድረስ እየተመለከትኩ ነበር ይላሉ ኢብን መስዑድ። ነገር ግን የመከልከል አቅም ስላልነበረኝ ምንም ላደርግ አልቻልኩም አሉ። ከዛም እነ አቡ ለሃብ መሳቅ እና መሳለቅ ጀመሩ፡ "ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) ሱጁድ ላይ እንደሆኑ ፋጢማ (ረ.ዐ) መጥታ ከላያቸው ላይ እስከታነሳላቸው ድረስ ቀና አላሉም ነበር።

ጭንቅላታቸውን ቀና ካደረጉ በኋላ ሦስት ጊዜ እንዲህ አሉ፡ "ጌታዬ ሆይ ቁረይሾችን ያዝ አድርግልኝ እያሉ ዱዓ ሲያደርጉባቸው፡ ሥጋት አደረባቸው፤ ምክንያቱም በዚያ በተቀደሰው ስፍራ የሚደረግ ልመና ምላሽ እንደሚያገኝ ያውቁ ስለነበር፤ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልመናቸውን ቀጠሉ ጌታዬ ሆይ፡ የአቡ ጀህልን፤ የዑትባ ቢን ረቢዓን፤ የሸይባ ቢን ረቢዓን፤ የአል-ወሊድ ቢን ዑትባ፤ የኡመያ ቢን ኸለፍን እና የዑቅባ ቢን አቢ ሙዓይጥን ጉዳይ ላንተ ትቸዋለሁ አሉ። ነፍሴ በእጁ በሆነችው አላህ እምላለሁ፤ በመልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ተቆጥረው ዱዓ የተደረገባቸው በሙሉ በበድር ጉድጓድ ላይ መገደላቸው የተደበቀ ታሪክ አይደለም።

> **<u>መልዕክት 3:</u>** አማኝ ሆይ፤ ለምን ተስፋ ትቆርጣለህ? አንተ ስትጠራው የሚሰማህ፤ ድክመትህን አይተው ሰዎች ሲከቡህ የሚደርስልህ አዛኝ የሆነ ጌታ እንዳለህ ማወቅ አለብህ። አንተ ችግር በገጠመህ ሰዓት ጭንቅላትህን ወደ ሰማይ ቀና አድርገህ ያረቢ ያረቢ በል። እርዳታንም ከጌታህ ፈልግ።

ለእርግጥም ከችግር በኋላ ምቾት አለ

የገባውን ቃል-ኪዳን ጠባቂ የሆነው አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል "ከችግርም በኋላ ምቾት አለ፡ ከችግር ጋር በርግጥም ምቾት አለ። [አሽ-ሸርህ፡5-6]"

የሰው ልጆች ወደ ኋላ ተመልሰው ሕጎቻቸውን ይለውጡ ዘንድ የተፈቀደ ቢሆን እንኳን፣ ከአላህ የተገባ ቃል አይከሽፍም፣ የአላህ ሱናም አይቀየርም። ምክንያቱም የአላህ ቃል-ኪዳን የጊዜ እና የቦታ ወሰንን የሚሻገር ነው። የቀደሙት የረሱል ባልደረቦች ይህንን የቃል-ኪዳን ትርጉም የተረዱባቸው ጥቅሶች በተወረዱበት መጠን እንደማይቆሙ ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ፡ "አንድ ችግር ሁለት ምቾቶችን አያሸንፍም" አከለውም እንዲህ አሉ፡ "ችግር የእንሽላሊት ጉድጓድ ወስጥ እንኳን ገብቶ ቢደበቅ ምቾት ጉድጓዱ ውስጥ ገብቶ ያወጣዋል።"

ሁሉን ቻይ የሆነው አላህ እንዲህ ብሏል፡ "አላህንም የሚፈራ ሰው ከነገሩ ሁሉ ለእርሱ መግራራትን ያደርግለታል። [አጦላቅ፡ 4]"

እናም የአላህ ሱና የሚያስተምረን፡ መከራዎች በሚጠናከሩበት እና በሚባባሱበት ጊዜ ምቾት እና እፎይታ እንደሚመጣ ነው፣ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና ባልደረቦቻቸው በሕዝባቸው መካከል በመካ ሲቸገሩ በነበረበት ወቅት አላህ ከስደት በኋላ እንዴት እንዳዳናቸው እና ከጨለማ ሕይወት ነፃ እንዳወጣቸው አላየህምን?

እናም በአሕዛቦች መካከል፣ ልባቸው ተጨንቆ ወደ ጉሮሯቸው በደረሰ ጊዜ፡ ሰዎች በአላህ ላይ መጥፎ ጥርጣሬዎችን በጠረጠሩ ጊዜ፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህችን እውነተኛ ንግግር ተናገሩ "አሁን እኛ ነን የምንወራቸው እነርሱ አይወሩንም" ብለዋል። እናም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሲያርፉ የረሱል ባልደረቦች አገር ምድሩ ጠበባቸው፣ ዐረቦችም ከሀዲ ሆኑ፣ አደጋም ተቀሰቀሰ ምንም እንኳን ከቀኖች ባያልፍም፣ በመጨረሻም ጭንቀቱ ረገፈ፣ ሙስሊሞችም የፋርስን እና የሮማውያን ወታደሮችን በመማረክ ወደ ድል አድራጊነት ተመለሱ፣ ከዚያም አላህ ፈቅዶ የተማረኩት ከሙስሊሞች ጎን ተሰልፈው እስኪዋጉ ድረስ ነበር የዘለቁት።

በታሪክ ውስጥ ያሉ ትምህርቶቹ አያልቁም፣ ጉዳዩ ከላይ ሲታይ መጥፎ ሊሆን ይችላል፣ ከዚያ ውጤቱ በአላህ ፈቃድ ጥሩ ይሆናል፣ አላየህም እንዴ መጥፎ እና አስቀያሚ ሁኔታዎች ሲከሰቱ? ሆኖም ግን በጉዳዩ ላይ አላህ እንዲህ ይለናል "ለእናንተ ክፉ ነገር ነው ብላችሁ አታስቡት፡ በእውነቱ እሱ ለእናንተ መልካም ነገር ነው። [አን-ኑር፡11]"

እዚህ ላይ ሱራቃ ቢን ማሊክ (ረ.ዐ) ከነብዩ ጋር በተገናኘ በመጀመሪያው ቀን አሳቸውን ለመግደል ቆርጦ ነበር የተነሳው፣ በመጨረሻ የአላህ ፍላጎት ሆነና የእርሳቸው ታማኝ ወታደር ሆነ።

> <u>መልዕክት 4፡</u> ነገሮች ሲታዩ በተቃራኒው የሚሆኑ ቢመስሉም እንኳን በመልካም ተስፋ እንመልከታቸው። እንዲሁም ተስፋ መቁረጥን እና ብስጭትን መተው አለብን። የከውኑ አይነታ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) "በጥሩ ነገር ተስፋ አድርጉ፡ ታገኙታላችሁም" አላሉንም እንዴ በል የተስፋህን መስኮት ከፈት አድርግ አንተ ተስፋ የቆረጥክ፣ የተስፋህ ብርሃን የጨለመውን ክፍል እንዲያሸንፍ ፍቀድለት፣ የጨለማውን ክፍል ማዕዘናት በተስፋ ብርሃን ክሮች አንቆጥቁጥ።

❁❁❁◯❁❁❁

በሰነፍነት የተፈረጀው ቶማስ ኤዲሰን

ቶማስ ኤዲሰን የተወለደው እ.ኤ.አ. በ1847 በአሜሪካ ኦሃዮ፡ ሚላን የሚባል ሥፍራ ውስጥ ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን ለሦስት ወሮች ብቻ ነበር የተማረው። የትምህርት ቤቱ ዋና አስተዳዳሪ ሰነፍ እና የአዕምሮ ውስንነት ያለበት ልጅ ሆኖ አገኘሁት በማለቱ ከትምህርት ቤቱ እንዲባረር ተደረገ፣ ከዚያም ትምህርቱን እንዲቀጥል አልተፈቀደለትም!!

ሰነፍ፣ አካል ጉዳተኛ እና ኋላቀር ነው በሚል ሰበብ በትምህርት ቤቱ የተወገዘው ይህ ሰው፡ አንድ ሺ ዘጠና ሦስት (1093) የፈጠራ ባለቤትነት መብቶችን በስሙ አስመዝግቧል። ይህ መዝገብ አሁንም በአሜሪካን አገር ባለው የፈጠራ ባለቤትነት ቢሮ ተመዝግቦ ይገኛል።

ትምህርት ቤቱ ትምህርቱን አንዳይቀጥል ሲከለክለው፣ እናቱ ይህ በልጇ ላይ የተሰጠው ፍርድ አግባብነት የጎደለው እና የተሳሳተ መሆኑን ስለተገነዘበች በቤት ውስጥ ማስተማሯን ቀጠለች እና እሱም ለዕውቀት ከፍተኛ ፍቅር እንዳለው እንዲሁም በልጅነቱ ግልጽ የሆነ ብስለትን አሳይቷል። ኤዲሰን ከትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር እና አስተማሪዎቹ የበለጠ ብስለት ያለው እና አስተዋይ ልጅ ስለነበረ፡ ብዙ ቁጥር ያላቸው ጥያቄዎችን ይጠይቅ ነበር፡ ይህ የኤዲሰን አብዝቶ መጠየቅ ታዲያ የግንዛቤ እጦት እና የስንፍና ማስረጃዎች እንደሆኑ በማሰብ ነበር እንዲባረር የተደረገው። እውነታው ግን የልጁ አብዝቶ መጠየቅ የአዕምሮውን ንቃት እና የአስተሳሰብ ነጻነትን ነበር የሚያመለክተው።

በኬሚስትሪ መስክ ያደረጋቸውን ሙከራዎች በቤተ-ሙከራ ውስጥ ነበር የሚያከናውነው፤ በሚጠቀምበት ጊዜ እሳት ስለሚነድ እና እሳቱ ሊያቃጥለው ብሎም ሕይወቱን ሊያጠፋው ተቃርቦ የነበረበት ጊዜም አይዘነጋም፡ በመጨረሻም ይህ ክስተት የኤዲሰንን ልጅ መስማት የተሳነው እንዲሆን ዳረገው።

የመጀመሪያው የፈጠራ ሥራውን አንድ ብሎ የጀመረው ድምጽ ቀድቶ እንደገና ለመስማት የሚያገለግገ "gramophone" የተባለውን እቃ በማስገኘት ሲሆን በወቅቱ እጅግ ከፍተኛ መጠን በሚባል ዋጋ በአርባ ሺህ (40,000) ዶላር በመሸጥ ያሳለፋቸውን የድህነት፣ የረሃብ እና በቆሸሹ ስፍራዎች መተኛትን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናበታቸው። በመጨረሻም ለፈጠራ ሥራ ራሱን በመስጠት ኒውዮርክ ውስጥ ትልቅ ቤተ-ሙከራ ማቋቋም ቻለ፣ ይህም በዓለም ውስጥ ላሉት የቤተ-ሙከራ ኩባንያዎች እና ፋብሪካዎች ፈር ቀዳጅ ነበር።